ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን መምሪያ ቁጥር 1/2016

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን
# መምሪያ ቁጥር 1/2016

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን መምሪያ

## መግቢያ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 9(4) መሰረት ሀገሪቱ ያጸደቀቻቸው የሕጻናት መብቶችን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል እንደሆኑ በተጠቀሰው አግባብ ፍርድ ቤቶችን ጨምሮ በመንግስት አካላት የሚወጡ ህጎችን ከላይ ከተጠቀሱት ስምምነቶች ጋር የማጣጣም እና አሰራሮችን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ፍርድ ቤቶች የሕጻናት መብቶችን የማስከበር ወይም የመተግበር ግዴታ ካለባቸው አካላት ዋነኛ እንደመሆናቸው መጠን በሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) እንዲሁም በአፍሪካ የሕጻናት መብቶች እና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4(1) እንደሌሎቹ የመንግስት የስራ ክፍሎች ሕጻናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ

የሕጻናትን ጥቅም እና ደህንነት የሚያስጠብቅ አሰራር መዘርጋት እንደሚገባቸው በመመልከቱ፤

ፍርድ ቤቶች የሕጻናት የመኖር እና በምቹ ሁኔታ የማደግ መብት ሊያስጠብቁ የሚችሉ ግልጽ፣ ወጥ እና ተገማች የሆኑ የቀለብ ውሳኔዎች እንዲወስኑ የሚያግዝ ህግ እና አሰራር መዘጋጀት እንዳለበት ስለታመነ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ ቤት ይህንን የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን መምሪያ (ጋይድላይን) አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. የመምሪያው አጭር ርዕስ

ይህ መምሪያ “የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን መምሪያ ቁጥር 1/2016” ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

## 2. የቃላት ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መምሪያ

1. “ሕጻን” ማለት ከጽንስ ጀምሮ ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው ማለት ነው ፡፡
2. “ልዩ ፍላጎት” ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ እና ዋና ዋና እንደመተንፈስ፣ መስማት፣ ማየት፣ መናገር፣ መራመድ፣ ክንድ እና እጅን መጠቀም፣ መማር፣ መጫወት ወይም የመሳሰሉት የሕይወት እንቅስቃሴዎችን የሚገድቡ አካላዊ፣ ስሜታዊ ወይም አእምሯዊ ጉድለቶች በመኖራቸው ምክንያት ልዩ እንክብካቤ

የሚጠይቁ ሁኔታዎችን ያካትታል፡፡

3. “ፍርድ ቤት ወይም ፍርድ ቤቶች” ማለት በፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2(4) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
4. “ዳኛ ወይም ዳኞች” ማለት በፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀጽ 2(7) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
5. “ቀለብ” ማለት ቀለብ ሰጪ ለቀለብ ተቀባዩ የሚከፍለው ለሕጻኑ እንክብካቤ፣ ጥበቃ እና ጥቅም የሚውል በመሠረቱ በጥሬ ገንዘብ ወይም በልዩ ሁኔታዎች በአይነት የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
6. “የቀለብ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ” ማለት ቀለብ ከፋይ በየጊዜው ወይም በየወቅቱ ለቀለብ ተቀባይ የቀለብ ገንዘብ እንዲከፍል በፍርድ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ነው፡፡
7. “ገቢ” ማለት በፌደራል ገቢ ግብር

አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 2(14) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

8. “ቀለብ ከፋይ/ሰጪ” ማለት የሕጻናት ማሳደጊያ ለመክፈል የተስማማ ወይም በህግ ግዴታ ያለበት ወይም በፍርድ ቤት የሕጻናት ማሳደጊያ እንዲከፍል የታዘዘ ሰው ማለት ነው፡፡
9. “ቀለብ ተከፋይ/ተቀባይ” ማለት በፍርድ ቤት ቀለብ የተጠየቀለትን ሕጻን የሚያሳድግ ወላጅ፣አሳዳጊ ወይም ሞግዚት ነው፡፡
10. “የንግድ ቢሮ” ማለት በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የወረዳ፣ ክ/ከተማ፣ ከተማ ንግድ ጽ/ቤት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የፌደራል የንግድ ሚኒስቴር እና የክልል ንግድ ቢሮዎችን ያጠቃልላል፡፡
11. “ገቢዎች ቢሮ” ማለት በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ አነስተኛ፣

መካከለኛ እና ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ጽ/ቤቶች፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽንን ሲሆን የክልል ግብር አስከፋይ ጽ/ቤቶችን ያካትታል፡፡

12. “የፋይናንስ ተቋም” ማለት ባንክ ወይም እንደ ባንክ የሚሠራ ማንኛውም ተቋም ሲሆን ለዚህ መምሪያ አፈጻጸም በተቋም ደረጃ የተቋቋመ ብድር እና ቁጠባ ማህበርን ይጨምራል፡፡
13. “ተቀጣሪ” ማለት ራሱን ችሎ የሚሠራን የሥራ ተቋራጭ ሳይጨምር በሌላ ሰው መሪነትና ቁጥጥር ሥር ሆኖ አገልግሎት ለመስጠት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ያጠቃልላል፡፡
14. “ቀጣሪ” ማለት ቀለብ ሰጪውን ወይም ቀለብ ተቀባዩን ቀጥሮ ደመወዝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እየከፈለ የሚያሰራ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል መስሪያ ቤት ወይም ግለሰብን ያካትታል፡፡

3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መምሪያ በአንዱ ጾታ የተገለጸው ለሌላው ጾታ ያገለግላል፡፡

4. የመምሪያው ዓላማ

የዚህ መምሪያ ዓላማ በዋነኛነት የሕጻናትን ቀለብ የማግኘት መብት ያስጠበቀ ወጥነት እና ተገማችነት ያለው የቀለብ ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የሕጻናትን መብት እና ጥቅም ማረጋገጥ ሲሆን በተለይም፡-

1. ቀለብ የመስጠት የህግ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው አቅሙ በፈቀደ መጠን ቀለብ በመስጠት ለቀለብ ተቀባይ ሕጻን ተገቢውን ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ ፣
2. የሕጻናትን የመኖር እና ምቹ በሆነ ሁኔታ የማደግ መብት ለማረጋገጥ የሚያስችል የቀለብ መጠን እንዲወሰን ማስቻል፣
3. ፍርድ ቤቶች የሕጻናትን ቀለብ የሚመለከቱ ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ

ለመወሰን የሚያስችላቸውን ግልጽ አሰራር መዘርጋት፣

4. የሕጻናት አስተዳደግ በተለይም የሕጻናት ቀለብን በተመለከተ በወላጆች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ማዘጋጀት እና
5. ወላጆች የሕጻናት ቀለብ የሚወሰንበትን ሂደት በቀላሉ ሊረዱ የሚችሉበትን መንገድ መዘርጋት ነው፡፡

## 5. የመምሪያው የአፈጻጸም ወሰን

የዚህ መምሪያ ድንጋጌዎችን፡-

1. በፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጊዜያዊ ቀለብ ጥያቄዎችን ጨምሮ በየትኛውም የፍርድ ቤቱ እርከን የሚቀርቡ የሕጻናት ቀለብ ጉዳዮችን ለመወሰን ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. እድሜው ለአካለ መጠን የደረሰ ነገር ግን በበሽታ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሌላ

አሳማኝ ምክንያት ለህይወቱ አስፈላጊ ነገሮች ማግኘት ላልቻለ ሰው ቀለብ ለመወሰን ተፈጻሚ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

## 6. መርህ

የሕጻናት ቀለብ አወሳሰን፡-

1. በዋነኝነት የሕጻናት ጥቅም እና ደህንነት ቀዳሚ ማድረግ አለበት፡፡
2. ሕጻናት ወላጆቻቸውን የማወቅ እና ከወላጆቻቸው እንክብካቤ የማግኘት መብት ላይ መመስረት አለበት፡፡
3. ወላጆች አቅማቸው በፈቀደ መጠን ልጆቻቸውን የማሳደግና የመንከባከብ ህጋዊ ኃላፊነት ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ ወላጆች ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነታቸውን እንደየገቢያቸው መጠን ሊጋሩ እንደሚገባ ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት፡፡
4. በሕጻናት ቀለብ አወሳሰን ሂደት ወላጆች ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን መሰረታዊ የሆኑ ምግብ፣ መጠለያ እና አልባሳት ታሳቢ

ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም በየትኛውም ሁኔታ ግን ለሕጻናት ቀለብ የመስጠት ግዴታን የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡

5. የሕጻናትን መሠረታዊ ፍላጎቶችና ልዩ ወጪዎች ታሳቢ ማድረግ ያለበት ሲሆን ከወላጆቹ አንዱ የተሻለ ገቢ ያለው ከሆነ ሕጻኑ የዚህ ገቢ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡
6. በማስረጃ የተረጋገጠ ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ስራ ባለመስራት ወይም ገቢ ባለማግኘት ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡
7. የሕጻናቱን እድሜ፣ ብዛት፣ የጤና ሁኔታ፣ ልዩ ፍላጎት፣ የሁለቱም ወላጆቹን የገቢ እና ወጪ መጠን እና ተቀባይነት ያላቸው ወይም ህጋዊ ተቀናሾች ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡
8. ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ በመምሪያው መሰረት ከሚወሰነው የቀለብ መጠን በተጨማሪ ለመክፈል ፍቃደኛ

ከሆነ ወይም ይከፍል ከነበረ ይህንኑ ከግምት ማስገባት አለበት፡፡

9. በሕጻኑ ወላጆች የጋብቻ ሁኔታ የሚወሰን ባለመሆኑ የቀለብ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ መወሰን አለበት፡፡
10. ፆታዊ መድሎ የሌለበት መሆን አለበት፡፡
11. በወላጆች መሠረታዊ የኑሮ ሁኔታ ላይ የተጋነነ ችግር ማስከተል የለበትም፡፡ በተለይም የመምሪያው አፈፃፀም ወላጆች ሌላ ቤተሰብ እንዳይመሰርቱ፤ ወይም ስራ ሰርተው ገቢ እንዳያገኙ የሚገፋፉቸው መሆን የለበትም፡፡
12. ወላጆች በልጆቻቸው አስተዳደግ እና እንክብካቤ ላይ በጋራ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ በተቻለ መጠን ወላጆች የሞግዚትነት ኃላፊነትታቸውን በጋራ እንዲወጡ የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡
13. የዋጋ ግሽበት ወይም የኑሮ ውድነትን ወይም የሕጻኑ ፍላጎት መጨመርን ወይም የቀለብ ሰጪን የመክፈል አቅም

መለወጥን መሠረት አድርጎ ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

# ክፍል ሁለት

## በሕጻናት ቀለብ የሚሸፈኑ ወጪዎች

**7. የሕጻናት ቀለብ መሰረታዊ ወጪዎች**

ዳኞች የሕጻናት ቀለብ በሚወስኑበት ወቅት የሕጻኑን ምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ ጤና አጠባቅ እና ትምህርት ያሉ መሰረታዊ ወጪዎች እንዲሁም የሕጻኑን ልዩ ፍላጎት ከግምት ማስገባት አለባቸው፡፡

**8. የሕጻናት ቀለብ ውሳኔዎች የሚገቡ ሁኔታዎች**

1. ዳኞች የሕጻናት ቀለብ ሲወስኑ የቀለብ ተቀባይ ሕጻናት ብዛት፣ የኑሮ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ልዩ ፍላጎት  እና የጤና ሁኔታ እንዲሁም የቀለብ ሰጪውን እድሜ፣

አቅም፣ የገቢ እና የኑሮ ሁኔታ ማመዛዘን አለባቸው፡፡

2. ወላጆች አብረው ሕጻኑን ያሳድጉ ከነበረ ከመለያየታቸው በፊት ሕጻኑ የለመደውን የኑሮ ሁኔታ እና/ወይም የቀለብ ወጪ ያማከለ መሆን አለበት፡፡

## 9. በአይነት ቀለብ የሚሰጥበት ሁኔታ

1. የሕጻናት ቀለብ የሚከፈለው በጥሬ ገንዘብ ሲሆን በቀለብ ሰጪ ወይም ተቀባዩ አመልካችነት ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የሕጻናት ማሳደጊያ ቀለብ በአይነት እንዲሰጥ ሊወሰን ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ቀለብ በዓይነት እንዲሰጥ ለመወሰን የሚችለው ቀለብ የሚቀበለው ሕጻን ይኖርበት የነበረውን ሁኔታ እና የሕጻኑን ፍላጎት በማገናዘብ ቀለብ በዓይነት ካልተሰጠ በስተቀር የሕጻኑ ጥቅም እና ደህንነት በአግባቡ የማይጠበቅ ስለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ሲያገኝ ነው፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ለቀለብ ተቀባዩ ሕጻን የሚከፈለው ቀለብ በገንዘብ መስጠቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ሆኖ ካገኘው ይህንኑ በውሳኔው ላይ በማስፈር የቀለብ ክፍያ በአይነት እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል፡፡

## 10. ልዩ ወጪዎች

1. ፍርድ ቤቱ በቀለብ ጠያቂው ወይም በሕጻኑ አሳዳጊ ጥያቄ መሰረት ወይም በራሱ ተነሳሽነት በመምሪያው መሰረት ከሚሰላው የቀለብ መጠን በላይ የሕጻኑን ልዩ ፍላጎት ወይም አኗኗር ቅድሚያ በመስጠት የሚከተሉትን ተጨማሪ ወጪዎች በሙሉ ወይም በከፊል ቀለብ ሰጪው እንዲሸፈን መወሰን ይችላሉ፡፡

ሀ. ወቅትን ተከትለው ለሚመጡ ቀላል የጤና ችግሮችን ለመታከም እና መድሃኒት ለመግዛት የሚወጡ የሕክምና ወጪዎች ሳያካትት ድንገተኛ ህመም ለመታከም

ወይም ተከታታይ ህክምና ለማድረግ እና መድኃኒት ለመግዛት የሚወጡ ወጪዎችን፣

ለ. ልዩ ፍላጎት ላለው ሕጻን ጥቅም የሚሆን ማንኛውም የድጋፍ ቁሳቁስ ለመግዛት ወይም ባለሞያ ለመቅጠር የሚያስፈልግ ወጪ፣

ሐ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሕጻኑ ሞግዚት ለመቅጠር የሚያስፈልግ ወጪ፣

መ. የሕጻኑን የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት ከትምህርት ወይም ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጋር የተገናኙ ወጪዎች እና

ሠ. ለተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴዎች እና የሕጻናት መዝናኛ የሚወጡ ወጪዎች።

2. ፍርድ ቤቱ ልዩ ወይም ተጨማሪ ወጪዎች መወሰን እንደሚኖርበት ካመነ፣ የዚህ ልዩ ወጪ ያስፈለገበት ምክንያት፣ የሚከፈልበት ጊዜ፣ ክፍያው የሚያበቃበት የጊዜ ገደብ እና የሚከፈለውን የቀለብ

መጠን በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡

## 11. ሕጻናት የማሳደግ መብትን ስለ መጋራት

1. ቀለብ ለመቀበል መብት ያላቸው ሆነው በወላጆች መካከል ተለያይተው የሚያድጉ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሕጻናት ሲኖሩ የእያንዳንዱ ወላጅ ቀለብ የመክፈል አቅም መጠን ከተለየ በኂላ የሕጻናቱ የቀለብ መጠን የሚወሰነው እያንዳንዳቸው በሚከፍሉት መጠን መካከል ባለው ልዩነት ብቻ ነው፡፡

2. ቀለብ ሰጪ ሕጻኑን በዓመት ለተከታታይ ለ30 ቀናት ወይም ከዚያ ለሚበልጥ ጊዜ ለብቻው የሚያሳድግ ከሆነ እንዲከፍል ከተወሰነው የቀለብ መጠን ላይ ፍርድ ቤቱ ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ተቀናሽ ሊያደረግለት ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የቀለብ አሰላል ስርዓት፣ የሕጻናት ቀለብ ፍርድ ይዘት እና የቀለብ ውሳኔን ስለመለወጥ

**12. የቀለብ መጠን በመምሪያው መሰረት ስለመወሰን**

ቀለብ ከፋይ የሚከፍለው የቀለብ መጠን በዚህ መምሪያ አባሪ ላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ መሰረት መሰላት አለበት፡፡

**13. በቀለብ አሰላል ሰንጠረዥ ሳይገደቡ ልዩ ቀለብ ስለመወሰን**

1. ቀለብ ተቀባዩን ሕጻን የሚያሳድገው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤቱ ቀለብ ተቀባዩ ሕጻን ላይ ከባድ ችግር እንደደረሰበት ካረጋገጠ ወይም ከባድ ችግር ሊደርስበት እንደሚችል በቂ እና አሳማኝ በሆነ ማስረጃ ከተረጋገጠ በዚህ መምሪያ በተቀመጠው ሰንጠረዥ ሳይገደብ የቀለብ

መጠን መወሰን ይችላል፡፡

2. የቀለብ ተቀባዩ ሕጻን ወላጅ በተወሰነለት ቀለብ የሕጻኑን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት ወይም መሸፈን አለመቻል እንደከባድ ችግር ሊወሰድ ይችላል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ሕጻኑ ከባድ ችግር እንዳለበት እና በዚህ ምክንያት የተለየ የቀለብ መጠን መወሰን እንደሚኖርበት ካመነ፣ ልዩ ቀለብ ያስፈለገበትን ምክንያት፣ የሚከፈልበትን ጊዜ፣ ክፍያው የሚያበቃበት የጊዜ ገደብ እና የሚከፈለውን የቀለብ መጠን በውሳኔው ላይ በግልጽ ማስፈር አለበት፡፡

**14.** ከቀለብ አሰላል ሰንጠረዥ ውጪ ቀለብ ሊወሰንበት የሚቻልበት የቀለብ ሰጪ ልዩ ሁኔታዎች

1. ፍርድ ቤቱ በቀለብ ሰጪው አመልካችነት ቀለብ ሰጪው ከባድ ችግር እንደደረሰበት በቂ እና አሳማኝ በሆነ ማስረጃ ከተረዳ ይህንኑ ምክንያት በውሳኔ ላይ በግልጽ

በማስቀመጥ ያመነበትን ተገቢ ነው ያለውን የቀለብ መጠን ሊወስን ይችላል፡፡

2. ፍርድ ቤቱ የሕጻናት ቀለብ በመምሪያው ከተቀመጠው አሰላል ውጪ ለመወሰን በቀለብ ሰጪው ላይ ከባድ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉትን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡

ሀ. ቀለብ ሰጪ ለሕጻኑ እና ለቤተሰቡ ሲል መደበኛው ኑሮ ከሚጠይቀው በላይ ዕዳ ውስጥ ከገባ እና በዚህ ምክንያት የተወሰነው ቀለብ መክፈል ካልቻለ፣

ለ. ቀለብ ሰጪ በተጨማሪ ለሌሎች ሰዎች ቀለብ እየሰጠ ከሆነ እና ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ፣

ሐ. ቀለብ ሰጪ መንቀሳቀስ ወይም ሥራ መሥራት በማይችልበት ልዩ ሁኔታ ምክንያት በችግር ውስጥ መውደቁ ሲረጋገጥ፣

3. ከላይ በንዑስ ቁጥር 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ቢኖሩም ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ገቢ የለም በማለት በቀለብ ሰጪው አማካኝነት በሚቀርብ

ክርክር ላይ ተመስርቶ ቀለብ የመስጠት ግዴታን ሊያስቀር አይችልም፡፡

## 15. የቀለብ ውሳኔ ይዘት

ፍርድ ቤቱ የሕጻናት ቀለብ በጥሬ ገንዘብ መከፈል እንዳለበት የሚሰጠው ውሳኔ የተሟላ የሚሆነው የሚከተሉትን ጉዳዮች ሲያካትት ነው፡፡

1. የእያንዳንዱን የቀለብ ተቀባይ ሕጻናት ሙሉ ስም እና ዕድሜ፣
2. የቀለብ ሰጪው ጠቅላላ ገቢ እና የተጣራ ገቢ፣
3. የሕጻናት ብዛት ፣
4. መሰረታዊ ፍላጎት ለሟሟላት ያስፈልጋል ብሎ ያመነበት የወጪ መጠን
5. በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው መሰረት ልዩ ወጪዎች ካሉ፣
6. በአይነት የሚወሰን ቀለብ ተመጣጣኝ የገንዘብ ግምት፣
7. የመጀመሪያው ክፍያ የሚከፈልበት ፣

ቀጣይ ክፍያዎች የሚፈጸሙበት እና የቀለብ ክፍያ የሚያበቃበት ጊዜ እና

8. ቀለብ ጠያቂው የቀለቡ ገንዘቡ ሕጻኑን ለመንከባከብ ፣ ለመጠበቅ እና ደህንነቱን ለማስጠበቅ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤

## 16. የቀለብ ውሳኔን የሚቀይሩ ሁኔታዎች

1. ፍርድ ቤቱ አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ እንደ ሁኔታው የቀለብ መጠን ሊለወጥ፣ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል:: ሆኖም፣ የተወሰነውን የቀለብ መጠን ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ፍርድ ቤቱ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል ::
2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የቀለብ መጠንን ለመለወጥ እንደ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች ሊቆጠሩ ይችላሉ::

ሀ. የቀለብ ሰጪ ገቢ መጨመር ወይም መቀነስ፣

ሰ. የቀለብ ተቀባይ ሕጻናት ፍላጎት መጨመር ወይም መቀነስ፣

ሐ. የዋጋ ግሽበት፣

መ. የቀለብ መጠኑ በዚህ መምሪያ መሠረት አለመሰላት፣

ሠ. በዚህ መምሪያ አንቀጽ 13 እና 14 በተገለጹት መሰረት የከባድ ችግር መፈጠር ወይም ከባድ ችግር የፈጠሩ ልዩ ሁኔታዎች እንደተከሰቱ ማረጋገጥ ከተቻለ፣

ረ. የቀለብ መጠን ሲሰላ ልዩ ወጭዎች ለሕጻኑ እድገት ከሚያስፈልገው ወጪ የተለየ ወጪ የሚያስከትሉ ከሆነ ወይም የተለወጠ ነገር ካለ

## 17. የቀለብ ሰጪ እና ተቀባይ ገቢ እና ወጪን ስለማጣራት

1. ቀለብ ሰጪው እና ተቀባዩ ገቢያቸውን እና ወጪያቸውን በስምምነት አስልተው በጽሁፍ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

2. ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ቀለብ የሚቀበለውን ሕጻን ጥቅም እና ደህንነት እንደ ሚያስጠብቅ ካረጋገጠ በኋላ በስምምነቱ የቀረበውን ገቢ እና ወጪ መሠረት በማድረግ የቀለብ ክፍያውን መጠን ይወስናል፡፡
3. ቀለብ ሰጪው እና ቀለብ ተቀባዩ የገቢ መጠንን በሚመለከት ስምምነት ላይ ካልደረሱ ፍርድ ቤቱ በቀጣሪዎች ፣ተቀባይነት ባላቸው ባለሞያዎች እና ተቋማት፣በምስክሮች ወይም ሌላ አግባብነት ይኖረዋል በሚለው ማስረጃ አማካኝነት የቀለብ ሰጪን ገቢ በማጣራት ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ የቀለብ ሰጪን የመኖሪያ ወይም የስራ አድራሻ ወይም የገቢ እና ወጪ አቅም ለማወቅ ማንኛውም መረጃ ይሰጣል ብሎ የገመተውን ሰው አስቀርቦ ሊመረምር ይችላል፡፡

## 18. ቀለብ የሚከፈልበት የገቢ ምንጭ

1. ቀለብ ሰጪው ተቀጥሮ ገቢ የሚያገኝ ተቀጣሪ ከሆነ ገቢው የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

ሀ) ደመወዝ፣

ለ) ለተጨማሪ ሥራ የሚከፈል ክፍያ፣

ሐ) ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ የሚቀበለው ክፍያ፣

መ) ጉርሻዎች፣

ሠ) የተለያዩ አበሎች፣

ረ) የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያዎች እና

ሰ) ከቅጥር ጋር የተያያዘ ሌላ ማንኛውም ገቢ

2. ቀለብ ሰጪው የራሱን ስራ የሚሰራ ከሆነ ገቢው የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሀ) ጠቅላላ ወርሃዊ ወይም አመታዊ ገቢ፣

ለ) በተለያዩ ቦታዎች ለሚሰራው ሥራ የሚከፈለው ክፍያ እና

ሐ) ከግል ሥራ የሚገኝ ሌላ ገቢ

3. ቀለብ ሰጪው ጡረተኛ ከሆነ፡-

ሀ) የጡረታ አበል እና

ለ) ማንኛውም ሌላ ገቢ ያካትታል፡፡

4. ቀለብ ሰጪው ጡረተኛ በሚሆንበት ወቅት ገቢውን ግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢውን ቀለብ በመወሰን የሕጻኑን ጥቅም እና ደህንነት መጠበቅ ይገባል፡፡
5. ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በማንኛውም የሥራ ሁኔታዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ገቢዎች በመጨመር በገቢ ውስጥ ማካተት ይቻላል፡፡

ሀ) ከቤት ኪራይ ወይም ሽያጭ ገቢ፣

ለ) ከተሽከርካሪ ኪራይ ወይም ሽያጭ ገቢ፣

ሐ) ከሌሎች ንብረቶች ሽያጭ የተገኘ ገቢ፣

መ) የባንክ ተቀማጭ ገንዘብ ወይም ብድር፣

ሠ) ባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ የሚገኝ ወለድ፣

ረ) ከሎተሪ እና ከተለያዩ ውድድሮች የሚገኝ

ገቢ ወይም የገንዘብ ሽልማቶች

ሰ) የካሳ ክፍያዎች እና

ሸ) ሌላ ማንኛውም ገቢ

6. ፍርድ ቤቱ የቀለብ ሰጪን የተጣራ ገቢ ለማወቅ ለቀጣሪ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት፣ ለገቢዎች ጽ/ቤት፣ ለንግድ ጽ/ቤት፣ ለባንክ ወይም ጉዳዩን ለማጣራት ተገቢ ነው ላለው ለማንኛውም አካል ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

## 19. ልዩ ሁኔታ

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የቀለብ ሰጪን ወይም ተቀባዩን ገቢ ማስላት ወይም ማወቅ ካልተቻለ፣ ቀለብ ጥያቄ የቀረበው የወላጆች መለያየትን ተከትሎ ከሆነ የወላጆች መለያየት ከመፈጠሩ አስቀድሞ

በቤተሰብ ውስጥ የሚወጣ የቀለብ ወጪ ላይ በመመስረት ፍርድ ቤቱ ከቀለብ አሰላል ሰንጠረዥ ውጪ ውሳኔ ላይ መድረስ ይችላል።

# ክፍል አራት

## የቀለብ ሰጪ እና የቀለብ ተቀባይ ግዴታ

### 20. የቀለብ ተቀባይ ግዴታ

1. ቀለብ ተቀባዩ ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው የቀለብ ጥያቄ ማመልከቻ

ሀ. የቀለብ ሰጪን የታወቁ የገቢ ምንጮች እና

ለ. ለሕጻኑ አስተዳደግ የሚያስፈልጉ ዝርዝር ወጪዎች የያዘ መሆን አለበት።

2. ቀለብ ተቀባዩ ቀለቡን ሕጻኑን ለመንከባከብ ፣ለመጠበቅ እና ደህንነቱን ለማስጠበቅ የመጠቀም ግዴታ አለበት።

## 21. የቀለብ ሰጪ ግዴታ

1. ቀለብ ሰጪው ገቢውን በተጠየቀው ትክክለኛ መንገድ መረጃ በመስጠት ለውሳኔው ወቅታዊነት እና ፍትሃዊነት አስተዋፅዖ ማድረግ አለበት፡፡
2. ቀለብ ሰጪ በፍርድ ቤቱ ሲጠየቅ ሁሉንም የገቢ ምንጩን እና ወጪውን በመሃላ ቃል ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ቀለብ ሰጪው የተወሰነውን ቀለብ በወቅቱ እና በታዘዘው ቦታ መክፈል አለበት፡፡
4. ቀለብ ሰጪው እንዳይሰራ የሚያግደው የጤና ችግር ከሌለበት ስራ የመስራት እና የተወሰነበትን የቀለብ ገንዘብ መክፈል አለበት፡፡

## 22. ቀለብ ሰጪ መረጃ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ

ቀለብ ሰጪ በአንቀጽ 21 መሰረት የሚጠየቀውን የገቢ መረጃ በአጭር ቀናት

ውስጥ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 23. ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት አለመቻል ወይም መረጃ አለማቅረብ

1. ቀለብ ሰጪ ያለ በቂ ምክንያት ማቅረብ የሚጠበቅበትን መረጃ ማቅረብ ካልቻለ ወይም ትክክለኛ መረጃ ካልሰጠ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽት ወይም በቀለብ ጠያቂው አመልካችነት ቀጣዮቹን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

ሀ. ቀለብ ሰጪ ያላቀረበውን መረጃ ለፍርድ ቤቱ እና ለቀለብ ተቀባይ እንዲያቀርብ ማዘዝ፣

ለ. ቀለብ ሰጪ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት በክርክሩ ውስጥ በሌላኛው ወገን የወጡትን ወጪዎች እንዲሸፍን ማዘዝ፣

ሐ. ቀለብ ጠያቂው በሚያቀርበው አቤቱታ መሰረት ሊሰጠው የሚገባውን ቀለብ መወሰን ወይም

መ. ቀለብ ሰጪ ትክክለኛ የገቢ መረጃ ባላቀረበበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ተገቢ ያለውን እርምጃ መወሰድ ይችላል፡፡

# ክፍል አምስት

# የሕጻናት ቀለብ ውሳኔ አፈጻጸም

## 24. የቀለብ ውሳኔ የሚወሰንበት ጊዜ

ፍርድ ቤቱ ለቀረበለት የቀለብ ጉዳይ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ጉዳዮች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 008/2013 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## 25. የቀለብ ውሳኔ ለማስፈጸም ስለሚሰጡ ትዕዛዞች

1. ፍርድ ቤቱ የሕጻናት ቀለብ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔውን ተፈጻሚነት እንዲኖረው እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ትዕዛዞች

መስጠት ይችላል።

ሀ) ቀለብ ሰጪ የተወሰነበትን የቀለብ ገንዘብ በቀለብ ተቀባይ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርግ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲሰጥ፣

ለ) የቀለብ ሰጪ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጣሪ ከሆነ መስሪያ ቤቱ ከቀለብ ሰጪ የወር ደመወዝ ላይ የቀለብ ገንዘብ ተቀናሽ አድርጎ ለቀለብ ተቀባይ እንዲከፍል፣

ሐ) ቀለብ ሰጪ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አሰሪው ከወር ደመወዙ ላይ እንዲቀንስ እና ለቀለብ ተቀባይ እንዲከፍል ወይም

መ) ሌላ ለሁኔታው ተገቢ የሆነ ትዕዛዝ፣

2. ተቀጣሪ ያልሆኑ ቀለብ ከፋዮች ላይ የተሰጠ የቀለብ ውሳኔን በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ለማስፈጸም ብቁ ነው የሚለውን አካል በመለየት እንዲተገበር ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

26. ቀለብ አለመክፈል ፣ ማዘግየት ወይም ማደናቀፍ

1. ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ ቀለብ ከፋይ የቀለብ ክፍያ አለመክፈል፣ ማዘግየት ወይም መጓተት እንደሌለበት ማስገንዘብ አለበት፡፡
2. የቀለብ ክፍያ ሳይከፈል ሲቀር ወይም ሲዘገይ ፍርድ ቤቱ ቀለብ ጠያቂው ሕጻን ጉዳት እንዳይደርስበት አቤቱታ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት እንደጉዳዩ አግባብነት

ሀ. ቀለብ ሰጪ ከአንድ ወር በላይ የሆነ የቀለብ ገንዘብ እንዲያሲዝ ወይም ተቀማጭ እንዲያደርግ፣

ለ. የቀለብ ሰጪ ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ እና ለቀለብ ክፍያ እንዲውል ወይም

ሐ. የቀለብ ሰጪ ደመወዝ ወይም ጥቅማ ጥቅም፣ በባንክ ያለ ገንዘብ ወይም ማንኛውም ከሶስተኛ ወገን የሚቀበለው ክፍያ እንዲያዝ ወይም እንዲከበር እና ለቀለብ ክፍያ እንዲውል

ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

3. ቀለብ ሰጪ የቀለብ ግዴታውን በወቅቱ አለመወጣቱን ፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥ ቀለብ በወቅቱ ስለመክፈሉ በቂ ዋስትና እንዲጠራ ማድረግ ይችላል፡፡
4. ቀለብ ሰጪ ላዘገየበት ተገቢውን ወለድ እና ቅጣት እንዲከፍል ሊወስን ይችላል ፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**27.** የመተባበር ኃላፊነት

ቀለብ ከፋይ፣ቀለብ ጠያቂ እንዲሁም ማንኛውም ሰው ለቀለብ አወሳሰን ሂደት የሚጠበቅባቸውን በማከናወን የቀለብ ጉዳዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት እንዲያገኙ የመተባበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 28. የሕጻናት ተሳትፎ እና የባለሞያ ሚና

1. ፍርድ ቤቱ የሕጻናት ቀለብ ሲወስን አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ የሕጻኑን ሀሳብ እና ፍላጎት በማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያ አማካኝነት መጠየቅ ወይም ማጣራት ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ፍትሐዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምትክ ዳኛ በመሾም ማስረጃ እንዲሰባሰብ ማድረግ ይችላል፡፡

## 29. በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች

ይህ መምሪያ ሥራ ላይ ሲውል በሂደት ላይ ያሉ የሕፃናት ቀለብ ክፍያን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ዳኞች በዚህ መምሪያ መሠረት ሊመሩ ይችላሉ፡፡

## 30. መምሪያውን ስለማሻሻል

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን መምሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም

ወቅት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**31.** መምሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መምሪያ ከነሐሴ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የሁለት ወራት የዝግጅት ጊዜ ሊኖረው ይችላል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ 2016 ዓ.ም

ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ፕሬዝዳንት

# የሕጻናት ወርሃዊ የቀለብ አወሳሰን የስሌት ሰንጠረዥ

| የቀለብ ሰጪ ወርሃዊ ገቢ (በብር) | 1 ሕጻን | 2 ሕጻናት | 3 ሕጻናት | 4 ሕጻናት | 5 ሕጻናት እና በላይ |
|---|---|---|---|---|---|
| እስከ 2,000 | 24% | 36% | 42% | 45% | 48% |
| 2,001-3,500 | 23.238% | 34.666% | 40.38% | 43.238% | 46% |
| 3,501-5,000 | 22.814% | 33.925% | 39.481% | 42.259% | 44.944% |
| 5,001-6,500 | 22.524% | 33.417% | 38.396% | 41.587% | 44.219% |
| 6,501-8000 | 22.239% | 33.031% | 37.935% | 41.078% | 43.67% |
| 8,001-9,500 | 22.051% | 32.71% | 37.553% | 40.657% | 43.218% |
| 9,501-11,000 | 21.894% | 32.442% | 37.235% | 40.307% | 42.84% |
| 11,001-12,500 | 21.76% | 32.213% | 36.962% | 40.00% | 42. 517% |
| 12,501-14,000 | 21.642% | 32.013% | 36.724% | 39.745% | 42.236% |
| 14,001-15,500 | 21.539% | 31.835% | 36.513% | 39.512% | 41.986% |
| 15,501-17,000 | 21.439% | 31.67% | 36.318% | 39.297% | 41.755% |
| 17,001-18,500 | 21.349% | 31.52% | 36.141% | 39.103% | 41.546% |
| 18,501-20,000 | 21.266% | 31.383% | 35.979% | 38.925% | 41.355 |
| 20.001-30,000 | 21.2% | 31.196% | 35% | 37% | 39% |
| 30,001-50,000 | 21.1% | 31.1% | 34% | 36% | 38% |
| 50,001-100,000 | 21.05% | 31% | 33% | 35% | 37% |
| 100,001-200,000 | 21% | 30% | 32% | 34% | 35% |

የቀለብ ሰጪ ወርሃዊ ገቢ ከብር 200,000 በላይ በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ የሕጻኑን ፍላጎት ባማከለ መልኩ በሰንጠረዡ ከተመለከተው የክፍያ መጠን ሳያንስ ሊወሰን ይችላል፡፡

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

# ስካን በማድረግ ያግኙን
# Scan and contact us on